# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ5 ዓመት (1998 - 2002) የልማት ዕቅድ

*የሚመለከታቸውን አካላት ግንዛቤ ለማዳበር አጥሮ*
*የተዘጋጀ ሰነድ*
***(Popular Version of PASDEP)***


## ፖቨርቲ አክሽን ኔትዎርክ ኦፍ ሲቪል
## ሶሳይቲ ኦርጋናይዜሽንስ ኢን ኢትዮጵያ
## (ፖአኔኢ)



**ታህሳስ 2000**
**አዲስ አበባ**

# 1. መግቢያ

በድህነት ቅነሳ ተግባር ላይ የሚንቀሳቀሱ የኢትዮጵያ የሲቪል ማሕበራት ጥምረት (PANE) አማካኝነት የድህነት ቅነሳና ዘላቂ ልማት ሂደቱ የሚመለከታቸውንና የጉዳዩ ባለድርሻ የሆኑትን የሕብረተሰብ ክፍሎች እንዲሁም የተለያዩ አስፈጻሚ አካላትን ግንዛቤ ለማዳበር ይህንን አጭር ሰነድ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። ሰነዱ በተለይ ትኩረት የሚሰጠው በአሁኑ ወቅት ፖለቲካዊ፣ አስተዳደራዊና ኢኮኖሚያዊ ውሳኔዎች ለሚሰጡባቸውና ለሚተገበሩባቸው ታችኛዎቹ የአስተዳደር ዕርከኖች ነው። አገሪቱ የምትከተለው ፌዴራሊዝም በአጠቃላይና በተለይም ያልተማከለ የፊስካል አስተዳደር ስርዓት ውሳኔ ሰጪነትን ከማዕከል ጉዳዩ ወደሚመለከታቸው ዝቅተኛ የአስተዳደር ዕርከኖች እንዲሸጋገር አድርጓል። ሁለተኛው ዙር ያልተማከለ አስተዳደር የማስፈን ፕሮግራም ከ1995 ዓ.ም የበጀት ዓመት ጀምሮ የወረዳዎችን በጀት በቀመር በመደልደል ወረዳዎቹም የተመደበላቸውን በጀት እንደየልማት ፍላጎቶቻቸው ቅደም ተከተል አውጥተው እንዲመድቡና እንዲጠቀሙ ሥልጣን ሰጥቷቸዋል። በመሆኑም ይህ አጠር ብሎ የተዘጋጀ ሰነድ በታችኛው እርከን ደረጃ ያሉ ዕቅድ አውጪዎች፣ አስፈጻሚዎችና ሌሎች አካላት የአገሪቱን ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች በሚገባ እንዲረዱና በልማት ዕቅድ ዝግጅትም ሆነ ክትትል ወቅት ጠቃሚ መነሻ አድርገው እንዲገለገሉበት ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል የሚል ፅኑ እምነትና ተስፋ አለን።

የዚህ አጭር ሰነድ ዋና ዓላማ ድህነትን ለማስወገድ የተዘጋጀውን የ5 ዓመቱን የፈጣንና ቀጣይነት ያለው የልማት ዕቅድ (PASDEP) ለመተግበርና ለመከታተል በሚያመች መልኩ አቀራረቡን ለተጠቃሚዎች ግልጽ እንዲሆን ማድረግ ነው። በዚህ ሰነድ የ5 ዓመቱን ዕቅድ ይዘት ጠቅለል ባለ ሁኔታ በማቅረብ ስለ ዕቅዱ አስፈላጊነት፣ መነሻ ሃሳቦች፣ ዓላማዎችና ዋና ዋና ስትራቴጂዎች በአጭሩ ለማብራራት ተሞክሯል።

# 2. የዕቅዱ መነሻዎች፣ ዓላማና ዋና ዋና ስትራቴጂዎች

## 2.1 የዕቅዱ መነሻዎች

የአሁኑ የ5 ዓመት ልማት እቅድ የተነደፈው ከ1995 እስከ 1997 ዓ.ም ተግባራዊ በተደረገው የዘላቂ ልማትና ድህነት ቅነሳ ፕሮግራም (SDPRP) ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ላይ በመመርኮዝ ነው። በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ራዕይ "በሚቀጥሉት 20 እና 30 ዓመታት ውስጥ በሕዝብ ተሳትፎና በሕዝቦች

መፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትና መልካም አስተዳደር የሰፈነባት፣ ማህበራዊ ፍትህ የነገሰባት፣ ከድህነት ተላቃ መካከለኛ ገቢ ያላት ኢትዮጵያን ዕውን ማድረግ ነው::" ይህ ዕቅድ ለምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች (MDGs) መዳረሻ ሆኖ የሚያገለግል የመጀመሪያው የ5 ዓመት የልማትና የድህነት ቅነሳ ዕቅድ ነው:: በኢኮኖሚው መስክ የአገሪቷ ራዕይ የሚከተሉትን አስቀምጧል::

- በከፍተኛ የቴክኖሎጂና ምርታማነት ደረጃ ላይ የደረሰ ዘመናዊ ግብርናና በኢኮኖሚው ውስጥ የመሪነት ሚናን መጫወት የሚቻልበት ደረጃ ላይ የደረሰ ኢንዱስትሪ ያለው ኢኮኖሚ የገነባች፣
- ፍትሐዊነት የተረጋገጠበትና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ ልማት እውን የሆነባት፣
- በዜጎች የነፍስ ወከፍ ዓመታዊ ገቢ ረገድ መካከለኛ ዕድገት ያላቸው አገሮች በደረሱበት ደረጃ ላይ የደረሰች አገር እንድትሆን ማስቻል የሚሉት ናቸው::

## 2.2 <u>የዕቅዱ ዓላማ</u>

የልማት ዕቅዱ ዋና ዓላማ የኢኮኖሚ ዕድገትን በማፋጠንና ዕድገቱ ቀጣይነት እንዲኖረው በማስቻል፣ ሕዝቡ በየደረጃው ተጠቃሚ የሚሆንበትንና ቢያንስ የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች ለማሳካት የሚያስችሉ አስተማማኝ የልማት ውጤቶች እንዲኖሩ ማድረግ ነው::

## 2.3 <u>የዕቅዱ ዋና ዋና ስትራቴጂዎች</u>

የኢትዮጵያ የ 5 ዓመቱ ዕቅድ የልማት ስትራቴጂዎች በሚከተሉት ዋና ዋና የስትራቴጂ አቅጣጫዎች/ምሰሶዎች ላይ የሚያተኩሩ ናቸው::

ሀ/ ሁሉን አቀፍ የማስፈጸም አቅም ግንባታ፣

ለ/ ፈጣን፣ መሠረተ ሰፊና ቀጣይነት ያለው ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ማስፈን፣

ሐ/ የሕዝብ ዕድገትና የኢኮኖሚ ዕድገትና ልማትን የማመጣጠን አቅጣጫ መከተል፣

መ/ የኢትዮጵያን ሴቶች ሁለንተናዊ አቅም ለመጠቀም የሚያስችል ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣

ሠ/ የአገሪቱን መሠረተ ልማታዊ መዋቅሮች ማጠናከርና ማስፋፋት፣

ረ/ የሰው ኃይል ልማትን አጠናክሮ መቀጠል፣

ሰ/ የሥራ ዕድል መፍጠር፣

ሸ/ የአደጋ ተጋላጭነት የሚያስከትለውን ስጋትና አለመረጋጋት መግታትና መቋቋም፣

### 2.3.1 ሁሉን አቀፍ የማስፈፀም አቅም መገንባት

መንግሥት ለዲሞክራሲ ግንባታው ሂደት ወሳኝ መንደርደሪያ ነው ብሎ ላመነበት የማስፈጸም አቅም ግንባታ ከልማት ስትራቴጂው ጋር የሚሄዱ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን ቀርጾ የሚጠናከሩበትንና ቀጣይነታቸው የሚረጋገጥበትን መርሐ ግብሮች ቀይሷል:: ለዚህም ዓላማ ከግብ መድረስ ዲሞክራሲያዊ ተቋሞችን ማጠናከር፣ የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያዎችን ማካሄድና የፍትሕ ሥርዓቱንም ማሻሻል ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው ታምኖበታል:: የወረዳ ደረጃ አቅም ግንባታ፣ የመረጃና ግንኙነት ቴክኖሎጂ ዕድገትና የኮንስትራክሽን ዘርፉን መደገፍም በዚሁ ሥር የሚጠቃለሉ ናቸው::

### 2.3.2 ፈጣን፣ መሠረተ ሰፊና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት ማስፈን

ፈጣን፣ መሰረተ ሰፊና ቀጣይነት ያለው ዕድገትን ለማፋጠን በሁለት አበይት ጉዳዮች ላይ ትኩረት ይደረጋል:: እነሱም፣

- ገበያ መር የግብርና ልማት፣ እና
- የግሉን ክፍለ ኤኮኖሚ ዕድገት ማፋጠን ናቸው::

ሀ/ <u>ገበያ መር ግብርና ልማትን ማፋጠን</u>

ገበያ መር የግብርና ልማትን እውን ለማድረግ የሚከተሉት ወሳኝ ሚና ይኖራቸዋል::

* እርሻና ገበያን የሚያገናኙና ክረምት ከበጋ የሚያገለግሉ መጋቢ መንገዶች መገንባት፣
* ለአነስተኛ ገበሬዎች ለግብርና ልማት የሚውል የብድር አገልግሎትን ማስፋፋት፣
* የተለያዩ የአገሪቱን የግብርና ሥነ ምህዳሮች ለሚወክሉ የልማት ቀጣናዎች/ዞኖች እና ዘመናዊ እርሻዎች የተለያዩ የግብርና ዘዴ (ኤክስቴንሽን) አገልግሎቶችን መስጠት፣
* አገር ዓቀፍ ይዘት ያለው የግብይት/የሥራ ዕቅድና ለውጪ ገበያ ለሚቀርቡ (እንደ ቅመማ ቅመም፣ አበባ፣ አትክልትና ፍራፍሬ ለመሳሰሉት) ሰብሎች ልማት የሚረዱ ተስማሚ ግብዓቶችን/ፓኬጆችን ማዘጋጀት፣
* ሁለገብ ግድቦችን በመጠቀም የመስኖ ልማትን ማስፋፋት፣
* የማዳበሪያና ምርጥ ዘር አቅርቦትን ማሻሻል፣
* የመሬት ይዞታ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚረዱ እርምጃዎች መውሰድና አመቺ በሆኑ አካባቢዎች ላይ ለሰፋፊ እርሻዎች የሚሆኑ ቦታዎችን ማዘጋጀት፣

ለ) <u>የግሉን ክፍለ ኢኮኖሚ ዕድገት ማፋጠን፣</u>

ለ.1) <u>የግለሰቦችን ተነሳሽነት ለመጨመርና ወደ ስራ ለመሳብ የአገልግሎት ተቋማትን ማጠናከር</u>

- የሥራ ፈቃድ አሠጣጥንና የሥራ ሂደት ቅልጥፍናን ማሻሻል፣
- የቁጥጥር ሥርዓቱን ማጠናከርና ምቹ ሁኔታን መፍጠር፣ ለዚህም የንብረት ባለቤትነትን በማረጋገጥ ረገድ የፍርድ ሂደትን ማሻሻል፣ ነጻ የሆነ የውድድር ሥርዓት መዘርጋትና የኮንትራት ውሎችን ተፈጻሚነት ማረጋገጥ፣
- የፋይናንስ ዘርፉን በማሻሻል የካፒታልና የሥራ ማስኬጃ ግኝት እንዲጨምር ማድረግ፣
- የግል ዘርፉ በአግባቡና በብቃት ሊያከናውናቸው የሚችላቸውን ሥራዎች ደረጃ በደረጃ ከመንግስት ወደ ግል በማስተላለፍ የወድድር መንፈስን ማስፈን፣
- የኢንቨስትመንትና የንግድ እንቅስቃሴዎችን በሚያበረታታ መልኩ የመሬት ይዞታ ዋስትና ቀጣይ ማሻሻያዎች ማድረግ፣
- መሠረተ ልማትን ማጠናከርና ማስፋፋት፣
- የትምህርት፣ የቴክኒክና የሙያ ፕሮግራሞችን በበለጠ በማስፋፋት የሰራተኛውን የሙያ ክህሎት ማሻሻል፣
- የማክሮ ኤኮኖሚውን በማረጋጋት፣ የምንዛሪ ሁኔታን በማመጣጠን፣ የዋጋ ንረትን መቆጣጠር /መግታት/፡፡

ለ.2) <u>የውጪ የገበያ ዕድሎችን መጠቀም</u>

በዚህ ረገድ የሚጠበቀውን ውጤት ለማስመዝገብ ቱሪዝምን ማስፋፋት፣ የእንስሳትን ሃብት ጥራት ላይ በማተኮር በሚገባ ማልማት፣ የአትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም የአበባ ምርቶችን በጥራትና በብዛት ማምረት፣ የጨርቃጨርቅና አልባሳት፣ አግሮ ኢንዱስትሪዎች እንዲስፋፉ ማገዝና የማዕድን ልማት እንዲካሄድ ይደረጋል፡፡

በዕቅዱ ጊዜ ማብቂያ ላይ (በ2002 ዓ.ም) የውጪ ንግድ ገቢን ወደ ታለመው ግብ ማለትም ከጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት ወደ ከ15-20% ለማድረስ በርትቶ መሥራት ይጠበቃል፡፡

## ሐ. <u>በጂኦግራፊ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ ስትራቴጅ መከተል</u>

አላስፈላጊ የሀብት ብክነትን ለመከላከልና ውጤታማ የልማት ሥራዎችን ለማከናወን የልማት ዞኖችን በጂኦግራፊ ሁኔታዎች (በአየር ንብረትና መሬት አቀማመጥ) በመከፋፈል ለየቦታው ተስማሚ በሆኑ የልማት እንቅስቃሴዎች ላይ መሰማራት፡፡

## መ. <u>የከተሞችን ዋና የልማት አጀንዳና የገጠርና ከተማ ቁርኝትን ማጠናከር</u>

- የማዘጋጃ ቤት አስተዳደርንና ሌሎች አስተዳደራዊ ተቋማትን ማጠናከር፣
- በአስፈላጊ የከተሞች መሠረተ ልማት ላይ መዋዕለ ንዋይን በማፍሰስ ልማትን ማፋጠን፣
- በመንግሥት በጀት ላይ ጫና የማይፈጠሩ ሌሎች የገንዘብ ምንጮችን መፈለግና መጠቀም፣
- የከተማ ቦታ አሰጣጥና አስተዳደርን በቀጣይነት ማሻሻል፡፡ ይህ ሁኔታ ለንግድ ሥራ ተነሳሽነትን ከመፍጠሩም ባሻገር ዋስትናን በማረጋገጥ ቤተሰቦችን ንብረት እንዲያፈሩ ሊያበረታታ ይችላል፡፡
- ለኢንዱስትሪ የሚሆኑ የከተማ ቦታዎችን ማስፋፋት፡፡ የገጠርና ከተማ ትስስሩን ማጠናከርና በቅንጅቱ መጠቀሙ የድህነት ቅነሳውን ሥራ ይረዳል፡፡ በዚህ ሂደት ገበያዎችን ማቀራረት፣ የሰው ኃይልን ዝውውር ነፃ ማድረግና የገቢ ማመንጫ እድሎችን ለከተሞችና በዙሪያቸው ለሚገኙ የገጠር አካባቢዎች ክፍት ማድረግ ይጠበቃል፡፡

## ሠ. <u>ለአርብቶ አደር አካባቢ ልዩ ትኩረት መስጠት</u>

በኢትዮጵያ ውስጥ በ7 ክልሎች ውስጥ የሚኖሩ ከ12 እስከ 15 ሚሊዮን የሚቆጠሩ አርብቶ አደሮች ይገኛሉ፡፡ አርብቶ አደሩ በአንድ ቦታ ረግቶ የማይቀመጥ በመሆኑ ለአገልግሎት አሰጣጥ ስለማይመች አካባቢው ድህነት ከማንኛውም ሥፍራ በከፋ መልኩ የተንሰራፋበት መሆኑ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም ይህ ዕቅድ በተለይ ለአርብቶ አደሩ የተዘጋጀ መርሐ ግብርን አካቷል፡፡ ትምህርትን በተመለከተ ለአኗኗር ስርዓታቸው ተስማሚና አመቺ የሆኑ የትምህርት አሰጣጥ ዘዴዎች እንዲዘጋጁላቸው ይደረጋል፡፡ የጤና አገልግሎት በአግባቡ እንዲያገኙ ተንቀሳቃሽ የጤና አገልግሎቶች ይዘጋጁላቸዋል፡፡ ለእንስሳት ሕክምና አገልግሎት፣ ለከብት እርባታ፣ ለግብይትና ለቅድመ ማስጠንቀቂያ ስርዓቶች ልዩ መርሐ ግብሮች እየተዘጋጁ ይገኛሉ፡፡ ለበጋ ጊዜ ንጹህ የመጠጥ ውኃ አቅርቦት እንዲኖር በአካባቢያቸው የውኃ አገልግሎት ተቋማት ይገነቡላቸዋል፡፡ መንገድ፣ መገናኛና አነስተኛ መስኖ የመሳሰሉ የመሠረተ ልማት

አውታሮች ተገንብተው ያሁኑን የኑሮ ሁኔታቸውን ከማሻሻልም ባሻገር ወደፊት አንድ ቦታ ረግተው መኖር ለሚመርጡት ልዩ ልዩ አገልግሎቶች ይመቻቹላቸዋል።

### 2.3.3 *የሕዝብ ብዛት ዕድገትና የኢኮኖሚ ዕድገትን ማመጣጠን*

ያለውን ብሔራዊ የስነ ሕዝብ ፖሊሲና ስትራቴጂ ተግባራዊ ለማድረግ ከሚደረገው ያላሰለሰ ጥረት ጐን ለጐን የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎትም ተጠናክሮ ይቀጥላል። ዕቅዱ የልጃገረዶች ትምህርትና ጎጂ ባሕላዊ ድርጊቶችን መዋጋት ለስነ ሕዝብ ፖሊሲ ዓላማና ግቦች መሳካት ወሳኝ ነው ብሎ ስለሚያምን ልዩ ትኩረት ይሰጠዋል።

### 2.3.4 *የኢትዮጵያን ሴቶች ሁለንተናዊ አቅም ለመጠቀም የሚያስችል ምቹ ሁኔታ መፍጠር*

- የዕቅዱ ዓላማ ሴቶች በብዛት ትምህርት ቤት ገብተው በመጨረስ በዕቅዱ ዘመን ማብቂያ ላይ ተሳትፏቸው ከወንዶች እኩል እንዲሆን ማድረግ ነው።
- የሴቶችን ጤና የሚንከባከቡ ሴት የጤና ባለሞያዎችን እስከ ቀበሌና ቤተሰብ ድረስ በማሰማራት የሴቶችን የጤና ሁኔታ ለማሻሻል ጥረት ይደረጋል። በመላ አገሪቱ ጤናማ ዕርግዝናና ወሊድን ለማረጋገጥ የሚያስችል መርሐ ግብር ይካሄዳል።
- በ2002 ዓ.ም የሕዝቡ 85% በግማሽ ኪሎ ሜትር ርቀት ውኃ እንዲያገኝ በማድረግ ከረጅም ርቀት ውኃ በመቅዳት የሚባክነውን የልጃገረዶችና የሴቶች ጊዜ መቆጠብ።
- በገጠር ለሴቶች አነስተኛ የሥራ ዕድል ሊፈጥሩ የሚችሉ መስኮችን ማጎልበት።
- ሰፋ ባሉ መርሐ ግብሮች ለሴቶች ጉዳይ ትኩረት በመስጠት እንደ እርሻ ኤክስቴንሽን፣ ጥቃቅን ብድሮች፣ የተፈጥሮ ሀብት አያያዝ፣ አነስተኛ የንግድ ሥራዎች በመሳሰሉት እንቅስቃሴዎች ላይ ምርታማነታቸውን ማሳደግ።
- የሴቶችን መብቶችና ዕድሎች የሚጠብቁና የሚያስከብሩ ሕግጋትና ተቋማትን የማሻሻሉን ተግባር አጠናክሮ መቀጠል።

### 2.3.5 የመሠረተ ልማት ግንባታን ማጠናከር

#### ሀ. የመንገድ አውታሮች

በዕቅዱ መሠረት እስከ 2002 ድረስ **20,000** ኪ.ሜ (**90%** ያህሉ በገጠር አካባቢዎች) የሚጠጋ አዲስ መንገድ ይሠራል። እንደዚሁም ካሉት

መንገዶች ውስጥ 84% ለሚሆኑት በጥሩ ሁኔታ አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ ጥገና ይደረግላቸዋል፡፡ (ለመንገድ ዘርፍ ዝርዝር ዕቅድ አባሪ 2ን ይመልከቱ)

## ለ. <u>የንፁህ መጠጥ ውኃ አቅርቦት</u>

በገጠር የንፁህ መጠጥ ውኃ አቅርቦትን በተመለከተ 2,133 ጥልቅ ጉድጓዶችና 14,908 ጥልቅ ያልሆኑ ጉድጓዶችን፣ 101,355 በእጅ የተቆፈሩ ጉድጓዶች፣ 404 ኩሬዎች፣ 556 የውሃ ማጠራቀሚያ ቦታዎች፣ 14 የገፀ ምድር ውኃ ምንጮች የማዘጋጀትና 11,065 ምንጮችን የማልማት ስራዎች ይከናወናሉ፡፡ በተጨማሪም 48,510 ተቋማት ላይ የመልሶ ማቋቋም ሥራዎች ይከናወናሉ፡፡ በመርሐ ግብሩ ለግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ልማትና ለደሃው የከተማ ነዋሪ ኑሮ መሻሻል አስተዋጽኦ የሚያደርጉ የ738 ከተሞች የውኃ ሥራዎች የጥናትና ዲዛይን ሥራ፣ የ514 ከተሞች የውኃ ተቋማት ግንባታና የ228 ከተሞች የውኃ አቅርቦት ተቋማት የመልሶ ማቋቋም ሥራዎች እንዲሰሩ ታቅዷል፡፡

## ሐ. <u>የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት</u>

በዚህ ዕቅድ ዘመን 5 ተጨማሪ አዳዲስ ትላልቅ ግድቦች ተገንብተው የኃይል ማመንጨት አቅምን በ668 ሜጋዋት ከፍ በማድረግ ጠቅላላ ሽፋኑንና የኃይል አቅርቦቱን በ3 እጥፍ ለማሳደግ ታቅዷል፡፡ የገጠር የኤሌክትሪክ አቅርቦትን በ1997 ዓ.ም ከነበረበት 16% በዕቅዱ ዘመን ማብቂያ ወደ 50% ለማድረስ መርሐ ግብር ተቀርጾ ስራው በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡

## መ. <u>ቴሌኮሙኒኬሽን</u>

ቴሌኮሙኒኬሽንን በተመለከተ በጋራ ሊሠሩ የሚችሉ ኢንቨስተሮችን ለመሳብ ከፍተኛ እንቅስቃሴ እየተደረገ ነው፡፡ በ1997 ዓ.ም ከነበረው የአገልግሎቱ ሁኔታ ጋር ሲነጻጸርም በ2002 ዓ.ም ለመድረስ የተያዘው ግብ እንደሚከተለው ነው፡፡ የመደበኛ ቴሌፎን ደንበኞችን ብዛት ከ620,000 ወደ 3.23 ሚሊዮን በላይ፣ የሞባይል ደምበኞችን ብዛት ከ410,000 ወደ 6.76 ሚሊዮን በላይ እንዲሁም የኢንተርኔት ደንበኞችን ብዛት ከ17,000 ወደ 193,000 ለማድረስ ታቅዷል፡፡

### 2.3.6 <u>የሰው ኃይል ልማትን አጠናክሮ መቀጠል</u>

መንግሥት በሚቀጥሉት 5 ዓመታት የሰው ኃይል ልማትን ለማጠናከርና የትምህርት ስፋትንና ጥራትን ለማሻሻል ጥረት ያደርጋል፡፡ የትምህርት ዕድልን በተመለከተ የህጻናትን በተለይም የሴት ልጆችን የመማር ዕድል የሚገድቡ ችግሮችን ለመፍታት ጥረት ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም የመሰረታዊ ጤና አገልግሎቱን በተፋጠነ ሁኔታ በማስፋፋት በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ ሁሉም የገጠር ነዋሪ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆን ለማስቻል ያሉትንም ሆነ አዲስ የሚገነቡትን የጤና ተቋማት አቅም በፈቀደ መጠን በመሳሪያ፣ በሰው ኃይልና በፋይናንስ ማጠናከር፡፡

### 2.3.7 <u>የሥራ ዕድልን ማስፋፋት</u>

የሥራ ዕድልን በማስፋፋት ረገድ መንግሥት ሁለት ዋና ዋና ተግባራት ይጠብቁታል፡፡

- የሕዝብ ቁጥር ዕድገት መጠንን መቆጣጠር እና፣
- የሰው ጉልበትን በብዛት የሚጠቀሙ ምርታማ ተግባራትን ማስፋፋት ናቸው፡፡

በመሆኑም በዚህ የዕቅድ ወቅት ለገጠር ልማት፣ ለኢንዱስትሪ፣ ለወጪ ንግድ፣ ለኮንስትራክሽንና ለሌሎች በርካታ የሰው ኃይል ፈላጊ ሥራዎች ልዩ ስትራቴጂያዊ ትኩረት ይሰጣቸዋል፡፡ በመካከለኛና አነስተኛ ተቋማት ልማት ላይም ትኩረት ይደረጋል፡፡

### 2.3.8 <u>የአደጋ ተጋላጭነት የሚያስከትለውን ስጋትና አለመረጋጋት መግታትና መቋቋም</u>

የአደጋ ተጋላጭነት በሚከተሉት 3 ደረጃዎች ሊገቱ ይገባል፡፡

- በሰብዓዊ ሃብት ደረጃ፤ በእህል ምርት መቀነስና በህመም ምክንያት በቤተሰብ ደረጃ የሚከሰት የምግብ ዋስትና ችግርን መቀነስ፣
- በኢኮኖሚ አመራር ደረጃ፤ በልማት ዕርዳታ ማሽቆልቆል፣ በነዳጅ ዋጋ መናር፣ በብሔራዊ ገቢ መቀነስና በሌሎች ተመሳሳይ ምክንያቶች የተነሳ በመንግስት በጀት ላይ የሚደርሰውን ጫና መቀነስ፣
- በአጠቃላይ ብሔራዊ ኢኮኖሚ ደረጃ፤ የአጠቃላይ አገር ውስጥ ምርት ውጣ ውረድን በመቀነስ እድገቱ ቀጣይነት ያለውና ለድህነት ቅነሳ አስተዋጽኦ በሚያደርግ መልኩ እንዲሆን ማድረግ፡፡

ለተጠቀሱት እርምጃዎች መፍትሄ ይሆኑ ዘንድም በቤተሰብ ደረጃ በአንድ የሰብል አይነት ላይ የተመሰረተ የአመራረት ልማድን በማስቀረት የእርሻ ምርት ዓይነቶችን ማስፋፋት እና ከእርሻ ውጭ ያሉ የገቢ ምንጮችን መፍጠር

(Diversification)፣ በውስን የምርት ዓይነቶች ላይ የተመሰረተውን የውጪ ንግድ በሌሎች ምርቶች ላይም እንዲያተኩር ማድረግ፣ የመስኖ ልማትን ማስፋፋትና በአገር ዓቀፍ ደረጃ የተረጋጋ የዕርዳታ ፍሰት እንዲኖር ስርዓት መዘርጋት::

## 3. <u>የዕቅዱ አጠቃላይ ኤኮኖሚያዊ መዋቅርና የዕድገቱ ዕይታ</u>

### 3.1 <u>አጠቃላይ የኢኮኖሚ ልማት</u>

ባለፈው የልማት ዕቅድ ወቅት በዓመት በአማካይ 6.4በመቶ የኢኮኖሚ ዕድገት ተመዝግቦ ነበር:: በአሁኑ ዕቅድ ጊዜ በዓመት በአማካይ ወደ 7 በመቶ ያህል እንዲያድግ ታቅዷል:: የመካከለኛ ጊዜ ዓላማው ኢንቨስትመንትን የሚያበረታቱ ሁኔታዎችን በመፍጠርና አመቺ ፖሊሲዎችን በመንደፍ ምርታማነትን ማሳደግና ብሎም ዕድገትን ማምጣት ነው:: ዋነኛ ግቦቹም አጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርትን ማሣደግ፣ የተረጋጋ አጠቃላይ የኢኮኖሚ ሁኔታ ማስፈን፣ ከፍተኛ የዋጋ ግሽበትን በማያስከትል መልኩ የገንዘብ አቅርቦትን ማስፋፋትና የተረጋጋ የውጪ ምንዛሪ ተመን እንዲኖር ማድረግ ነው::

በእቅዱ ዘመን የግብርና ግብዓቶች አቅርቦት ከፍ እንዲል ይደረጋል:: የኤክስቴንሽን መርሐ ግብሮችና የመስኖ ሥራም ይስፋፋሉ:: የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ በዓመት በአማካይ በ6.2 በመቶ ያድጋል ተብሎ ይጠበቃል:: ይህ ስኬት ዕውን የሚሆነው ግን የወጪ ንግድ ማስፋፊያ ፖሊሲዎች ከተተገበሩና የብድር አገልግሎቶች ከተስፋፉ ብቻ ይሆናል::

ጥቅል የአገር ውስጥ ኢንቨስትመንት በአማካይ 24 በመቶ ይደርሳል:: የምርቱ አብዛኛው እጅ እያደገ ወደ ቁጠባና ኢንቨስትመንት ስለሚሄድ ፍጆታ ከምርቱ ዕድገት መጠን ባነሰ መልኩ የሚጨምር ይሆናል:: ቁጠባ ከአጠቃላይ ምርቱ የነበረው የ3.7 በመቶ ድርሻ ወደ 13.1 በመቶ እንደሚያድግ ይጠበቃል:: የውጪ ንግድ ከአጠቃላይ ምርቱ ወደ 20 በመቶ እንደሚያድግ ሲጠበቅ የገቢ ንግድ ወደ 31 በመቶ ዝቅ እንደሚል ይጠበቃል::

### 3.2 <u>የመንግስት ገቢና ወጪ</u>

በዚህ ዕቅድ ዓመታት ማብቂያ ላይ ከግብር የሚገኝ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት በ1997 ዓ.ም ከነበረበት 12.5 በመቶ ወደ 17 በመቶ እንደሚያድግ ይጠበቃል:: የካፒታል ወጪው ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት የነበረው ድርሻ ከ11.5 በመቶ ወደ 16 በመቶ ከፍ እንዲልና በድህነት ቅነሳ ላይ ያነጣጠሩ ወጪዎች እንዲጨምሩ ታቅዷል::

### 3.3 <u>የውጪ ንግድና የውጪ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት</u>

በቡና መላክ ላይ ብቻ የተመሰረተ ጥገኝነትን ለመቀነስ የውጪ ንግድን በመጠንና በአይነት ለማስፋፋትና ለማበረታታት ጥረት ይደረጋል፡፡ ቡና ለተወሰነ ጊዜ ዋነኛ የውጪ ንግድ ምርት ሆኖ ሊቆይ ቢችልም በውጪ ንግድ ዕድሎች የበለጠ ተጠቃሚ መሆን እንዲቻል በአትክልትና ፍራፍሬ፣ በአበባ፣ ሥጋ፣ ቆዳና፣ በጨርቃጨርቅ ምርቶች ውጪ ንግድን ለማሳደግ ጥረት ይደረጋል፡፡ የኢንቨስትመንት ሕጉን በማሻሻል ለውጪ አገር ቀጥታ ኢንቨስትመንት የበለጠ ተስማሚ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ይደረጋል፡፡

### 3.4 የፋይናንስ ክፍለ ኢኮኖሚ

ባንኮች የአሰራር ዘመናዊነትንና የሥራ ብቃታቸውን የማሻሻል ጥረት አጠናክረው እንዲቀጥሉ ይበረታታሉ፡፡ የግል ባለሀብቶችን በተሻለ የፋይናንስ አቅርቦት የማገዙ ሥራ የሚቀጥል ይሆናል፡፡ በዚህ የዕቅድ ጊዜ ማብቂያ ላይ የግል ባንኮች የተቀማጭ ገንዘብና የብድር ድርሻ ወደ 33 በመቶ ከፍ እንደሚል ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የቁጥጥርና ክትትል አቅም እንዲጠናከር ይደረጋል፡፡ የአነስተኛ ብድርና ቁጠባ ተቋማት ሽፋን በተለይ በገጠሩ ክፍል እንዲስፋፋ ጥረት ይደረጋል፡፡

### 3.5 የገንዘብ ፖሊሲ

የገንዘብ ፖሊሲ ዋነኛ ዓላማ የዋጋና የውጪ ምንዛሪ ተመን መረጋጋትን ማስፈን ሲሆን በዕቅዱ ወቅትም አማካይ ዓመታዊ የዋጋ ንረት መጣኔ ከ8 በመቶ እንዳይዘል ይጠበቃል፡፡

### 3.6 ያልተማከለ የፊስካል አስተዳደር ሥርዓት

የመካከለኛው ጊዜ የበጀት ፖሊሲው ዓላማ ከቁጥጥር ውጪ የሆነ የበጀት ጉድለት ሳይከሰት እንደ ግብርና፣ የምግብ ዋስትናና ትምህርት ላሉ ቁልፍ ዘርፎች በጀት መጨመር ይሆናል፡፡ የበጀት ጉድለቱ ከአጠቃላይ ምርቱ 6.5 በመቶ እንዳይበልጥ ጥረት ይደረጋል፡፡ የግብርናና ለውጭ ገበያ የሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎች እድገትና የግብር ስርዓት ማሻሻያው የመንግሥት ገቢን እንደሚያሳድጉ ይጠበቃል፡፡

ለክልል መንግስታት የሚደረገው የበጀት ድጋፍ ቀመር የወጪ ፍላጎታቸውንና የበጀት አጠቃቀም አቅማቸውን በሚለኩ መረጃዎች ላይ ተመስርቶ በየጊዜው የሚሻሻል ይሆናል፡፡ ወረዳዎች የሚመደብላቸውን ጥቅል በጀት ያለ ጣልቃ ገብነት እንደየአካባቢያቸው የወጪ ፍላጎትና ቅደም ተከተል መድበው ይሰሩበታል፡፡ በዚህ ዕቅድ ወቅት መጨረሻ ላይ እያንዳንዱ ክልል ተገቢ የሆነ የወረዳ በጀት ክፍፍል ቀመር ይኖረዋል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ ወረዳዎች ከወረዳቸው ከሚመነጨው ገቢ አብዛኛውን ለራሳቸው ጥቅም እንዲያውሉ

ይደረጋል። ቀመሮቹ ለራስ ገቢ ማሳደግ ማትጊያዎች እንዲኖራቸው ይደረጋል። የኦዲት፣ ኢንስፔክሽንና ቁጥጥር ስርዓቶችም እንዲጠናከሩ ይደረጋል።

## 4. <u>የኢኮኖሚና የማህበራዊ ክፍላተ - ኢኮኖሚ ዕቅድ</u>

### 4.1 <u>ግብርናና ገጠር ልማት</u> (የኢትዮጵያ የግብርና ልማት ስትራቴጂ ዋና ዋና መሠረቶች)

ፍትሐዊ የመሬት አሰጣጥና አጠቃቀም መስፈኑን ማረጋገጥ፣ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ማውጣትና ተግባራዊ ማድረግ፣ የተለያዩ የአገሪቱን የግብርና ኢኮሎጂ ዞኖችን ያገናዘቡ የምርት፣ የክፍፍልና የግብይት ስርዓቶች እንዲኖሩ ማድረግ ያስፈልጋል። ገበሬዎችና አርብቶ አደሮች የተሻለ አንፃራዊ ጥቅም የሚያገኙባቸውን ሥራዎች እንዲሰሩ መንግሥት ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል። በአሁኑ ወቅት በግብርና ኤኮሎጂ ልዩነታቸው ላይ በመመስረት አገሪቱ በ6 የተለያዩ የእድገት ዞኖች ወይም ኮሪደሮች እንድትከፋፈል ተደርጓል። እነሱም 1. ጣና-በለስ አካባቢ፣ 2. ድሬዳዋን ማዕከል በማድረግ ምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ፣ 3. የስምጥ ሸለቆ አካባቢ፣ 4. ደቡብና ደቡብ ምዕራብ አካባቢዎች፣ 5. አዲስ አበባ አካባቢ እና 6. የሰፈራ ጣቢያዎች የልማት ማዕከላት ናቸው። እነዚህ የዕድገት ዞኖች እንደ ዕድገት ማዕከላት እንዲያገለግሉ የታቀደ ሲሆን ከነዚህ አካባቢዎች የሚገኙ ደረጃቸውን የጠበቁ ምርቶች ወደ ዓለም ገበያ እንዲገቡ አስፈላጊው ጥረት ሁሉ ይደረጋል።

### 4.2 <u>ትምህርት</u>

የ3ኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም (ESDP III) (1998 - 2002 ዓ.ም) አጠቃላይ ዓላማ የምዕተዓመቱን የልማት ግቦችና የብሔራዊ የልማት ዕቅዱን ግቦች ለማሳካት የሰለጠኑና ብቃት ያላቸው ሠራተኞችን በሚፈለገው ብዛትና ጥረት ማቅረብ ነው። (የአንደኛ ደረጃ የትምህርት ልማት ግቦችን አባሪ 3 ላይ ይመልከቱ)።

### 4.3 <u>ጤና</u>

ዕቅዱ የሚያተኩረው ከድህነት ጋር ተያያዥነት ባላቸው በሽታዎች፣ ተላላፊነት ባላቸው እንደ ኤች.አይ.ቪ ኤድስ፣ የሳምባ ነቀርሳ፣ ወባ ባሉና በተቅማጥ እና እናቶችና ሕፃናትን በሚያጠቁ በሽታዎች ላይ ይሆናል። በገጠር አካባቢዎች ላይ የበለጠ ትኩረት የሚሰጥ ሲሆን አገልግሎቶችን ከቋሚ የጤና ማዕከሎች ወደ ሕዝቡ ማለትም ወደ መንደሮችና ቤተሰብ ደረጃ ለማድረስ ጥረት ይደረጋል። በተጨማሪና በዋነኝነትም በሁሉም የጤና አጠባበቅ ዕርከኖች ላይ የፆታ እኩልነት ጉዳይ የሚካተት ይሆናል። ለተጨማሪ ዝርዝር አባሪ 4ን ይመልከቱ።

## 4.4 ቱሪዝም

ቱሪዝም እስካሁን በበቂ ሁኔታ ያልተጠቀምንበት ዘርፍ ቢሆንም በእቅዱ ዘመን ትኩረት ከሚሰጣቸው ዘርፎች አንዱ ይሆናል፡፡ የመንግስት የረጅም ጊዜ ራዕይ ኢትዮጵያን በ2012 አፍሪካ ውስጥ ከሚገኙ 10 ከፍተኛ የቱሪስት መዳረሻ አገሮች አንዷ ለማድረግ ሲሆን ይህም ለድህነት ቅነሳው እንቅስቃሴ ቱሪዝም አስተዋፅኦ እንዲኖረው የማድረግ ዓላማም አለው፡፡

## 4.5 የማዕድን ልማት

በዚህ ዘርፍ የዕቅዱ ስትራቴጂና ዓላማዎች የጂኦሎጂ ካርታ ሽፋንን ማሳደግ፣ አመቺ ሁኔታዎችን መፍጠር፣ የውኃ ጂኦሎጂን፣ የጂኦሎጂ ምህንድስናና የጂኦፊዚካል ጥናቶችን ማካሄድ፣ ቴክኒክን የሚያሻሽሉ ሠነዶችን ማዘጋጀት፣ ቴክኒካዊ ድጋፍ ማቅረብ፣ ሥልጠና መስጠትና አማካሪ ተቋማትን ማደራጀት ይሆናሉ፡፡

## 4.6 ሥነ-ሕዝብና ልማት

የሕዝብ ብዛት ዕድገት (በዓመት በ2 ሚሊዮን መጨመር) በሀብት ላይ ጫና ስለሚፈጥር ለድህነት ቅነሳ እንቅፋት ነው፡፡ የሕዝብ ብዛት ዕድገትን መቀነስ ለሴቶችና ሕፃናት ጤና አጠባበቅም አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡ የወሊድ መጠን መጨመርና የሞት መጠን መቀነስ ለሕዝብ ብዛት መጨመር ምክንያቶች ናቸው፡፡ አሁን ባለው ሁኔታ እያንዳንዷ ሴት በአማካይ 5.4 ልጆች ትወልዳለች፡፡ የዕድገት መጠኑም 2.73 በመቶ ነው፡፡ ይሁንና ሰዎች አነስ ያለ ቤተሰብ ስለሚሹ የወሊድ መቆጣጠሪያ አጠቃቀም እየተሻሻለ መጥቷል፡፡ በመሆኑም በተለይ በአዲስ አበባ በአንድ ቤተሰብ የሚወለዱ ልጆች ቁጥር እየቀነሰ መጥቷል፡፡ የሕዝብ ብዛት ፖሊሲው እ.ኤ.አ በ2015 የውልደት መጠንን ከ5.4 ወደ 4 ለመቀነስ፣ የወሊድ መከላከያ አጠቃቀምን በ44 በመቶ ለማሳደግና የእናቶችና ሕፃናትን ሞት መጠንን ለመቀነስ ያለመ ነው፡፡

## 4.7 መሠረተ ልማት

### 4.7.1 የውኃ አቅርቦትና ንፅህና አጠባበቅ

የዕቅዱ ዓላማ በ2002 ዓ.ም የንፁህ መጠጥ ውኃ አቅርቦትን እንደሚከተለው ለማሻሻል ነው፡፡ በ1.5 ኪ.ሜ ባነሰ ርቀት ውስጥ ንፁሕ ውኃ የማግኘትን ድርሻ ከ44 በመቶ ወደ 80 በመቶ፣ የከተማ ሕዝብ በግማሽ ኪ.ሜ ርቀት ውስጥ ንፁሕ የመጠጥ ውኃ የማግኘትን ድርሻ ከ80.6 በመቶ ወደ 92.5 በመቶ ለማሳደግ ታቅዷል፡፡ በተጨማሪም የመስኖ አጠቃቀምን አሁን ከሚገኝበት 5 በመቶ በዕቅዱ ዘመን ማብቂያ ላይ ወደ 8 በመቶ ለማሳደግ ታቅዷል፡፡

መፀዳጃን በተመለከተ በዕቅዱ ወቅት የመፀዳጃ ቤቶች አጠቃቀምን በማስፋፋት የገጠሩን ሽፋን ከ17.5 በመቶ ወደ 79.8 በመቶ የከተማውን ሽፋን ደግሞ ከ50 በመቶ ወደ 89.4 በመቶ ከፍ ለማድረግ ታቅዷል:: ለተጨማሪ ዝርዝር አባሪ 5ን ይመልከቱ::

### 4.7.2 <u>የኤሌክትሪክ ኃይልና ቴሌኮሙኒኬሽን</u>

የኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽንን ጠቅላላ ኃይል የማመንጨት አቅምን ከ791 ሜጋ ዋት ወደ 2,218 ሜጋ ዋት በማሣደግ በ2002 ዓ.ም በ3 እጥፍ ከፍ ለማድረግ ታቅዷል:: ስለቴሌኮሙኒኬሽን ዝርዝር ግቦች አባሪ 6ን ይመልከቱ::

### 4.7.3 <u>የኢንዱስትሪ ልማት</u>

በዕቅዱ ዘመን የኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ በየዓመቱ በአማካይ በ11.5 በመቶ እያደገ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ውስጥ አሁን ያለውን የ13.6 በመቶ ድርሻ በዕቅዱ ዘመን መጨረሻ ላይ ወደ 16.5 በመቶ ለማሳደግ ታቅዷል::

## 5. <u>የማስፈጸም አቅም ግንባታ</u>

ኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ የዜጐቿን ሕገ መግሥታዊ መብት የሚያከብር ግልጽ ተጠያቂነት ያለበትና ዲሞክራሲያዊ የሆነ አስተዳደር ለማስፈን ቁርጠኝነት አሳይታለች:: በመሆኑም የልማት እቅዱን በአግባቡ ለመተግበር ሀገሪቱ የተለያዩ ስትራቴጂዎችንና በርካታ የማሻሻያ ፕሮግራሞችን ነድፋ በመንቀሳቀስ ላይ ትገኛለች::

### 5.1 <u>የገጠር ወረዳ አቅም ግንባታ</u>

በዕቅዱ ዘመን በወረዳ ደረጃ ያልተማከለ አስተዳደርን ለማጠናከር ትኩረት የተሰጣቸው ጉዳዮች የሚከተሉት ናቸው::

- የወረዳዎችን የሰው ኃይል ፍላጐት መለየት፣ ማሟላትና ማልማት፣
- ብቁ አደረጃጀት ያላቸው የወረዳ አስተዳደር ተቋማትን መዘርጋት፣
- ሕዝቡ በሰፊው እንዲሳተፍ አመቺ የሆነ ስርዓት መዘርጋት፣
- የወረዳ ጥቅል በጀት አመዳደብ፣ አጠቃቀምና ቁጥጥር ስርዓቶችን ማሻሻልና የወረዳ ዕቅድ አዘገጃጀትና አፈፃፀም ብቃትን ማጠናከር፣
- ግልጽነትና ተጠያቂነት ያላቸው የአገልግሎት አሰጣጥ አመልካቾችና የመገምገሚያ ስልቶችን ማዘጋጀት፣
- የቀበሌዎችን የማስፈጸም ዓቅም በሁሉም ዘርፎች መገንባት::

## 6. <u>የአካባቢ ጥበቃና ልማት</u>

አካባቢ ጥበቃን በተመለከተ ዋናው ጉዳይ አካባቢያዊ ዘላቂነትን ማረጋገጥ ሲሆን የአካባቢ ጥበቃ ዘርፍ ዋና ዋና ግቦች የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ/ ለዘላቂ ሕይወት የገጠር አካባቢን ማሻሻል፣

ለ/ የቆሻሻ አያያዝና ማስወገጃ ሥርዓትን ማሻሻልና ብክለትን መቀነስ፣

ሐ/ አካባቢያዊ ዘላቂነት ያለው ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ዕውን ማድረግ፡፡

## 7. <u>የልማት ዕቅዱ የክትትልና ግምገማ ስልቶች</u>

የልማት ዕቅዱ የክትትልና ግምገማ ስርዓት የሚከተሉትን ያካትታል፡፡

- ልዩ የዳሰሳ ጥናቶች ማድረግ፣
- የግብዓቶችና የውጤቶችን አካሄድ የሚያሳዩ ጠቋሚ መስፈርቶችን ማዘጋጀት፣
- እንደ አሳታፊ የድህነት ዳሰሳ ያሉ አዳዲስ ዘዴዎችን ሥራ ላይ ማዋል፣
- በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችና በክልል መንግስታት ዕርከኖች የሚሰበሰቡ መደበኛ መረጃዎችን መጠቀም፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት ምንጮች በተጨማሪ በሲቪል ማሕበረሰብ በሚሰበሰቡ ለምሳሌ በቅርቡ በPANE የተካሄደው የዜጎች ሪፖርት ካርድ የመሳሰሉ ጥናታዊ መረጃዎችን መጠቀምም ጠቃሚ ነው፡፡

## አባሪ 1፡ የ5 ዓመት የልማት ዕቅድ ዋና ዋና ግቦች (Targets)

| ዘርፍ/ግብ ወይም አመልካች | በ1997 መጨረሻ የተደረሰበት | የ5 ዓመቱ ዕቅድ ግብ (በ2002 መጨረሻ የሚደረስበት) |
|---|---|---|
| **አጠቃላይ ኢኮኖሚ** | | |
| ጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት (GDP) ዕድገት | **10.6** | ቢያንስ 7 በመቶ (አማካይ ዓመታዊ ዕድገት) |
| ጠቅላላ የአገር ውስጥ ኢንቨስትመንት ከጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት የሚኖረው ድርሻ (በመቶኛ) | **20.5** | **26.1** |
| ጠቅላላ የአገር ውስጥ ቁጠባ ከጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት የሚኖረው ድርሻ (በመቶኛ) | **3.7** | **13.1** |
| ጠቅላላ የውጪ ንግድ ከጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት በጊዜው የገበያ ዋጋ የሚኖረው ድርሻ (በመቶኛ) | **15.8** | **19.7** |
| ጠቅላላ የገቢ ንግድ ከጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት በጊዜው የገበያ ዋጋ የሚኖረው ድርሻ (በመቶኛ) | **34.3** | **31.7** |
| የአገር ውስጥ ገቢ ከጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት በጊዜው የገበያ ዋጋ የሚኖረው ድርሻ (በመቶኛ) | **15.8** | **18.7** |
| የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት በጊዜው የገበያ ዋጋ የሚኖረው ድርሻ (በመቶኛ) | **12.5** | **17** |
| ጠቅላላ የመንግሥት ወጪ ከጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት በጊዜው የገበያ ዋጋ የሚኖረው ድርሻ (በመቶኛ) | **25.2** | **27.0** |
| አጠቃላይ ድህነት ተኮር ወጪ ከጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት በጊዜው የገበያ ዋጋ የሚኖረው ድርሻ (በመቶኛ) | **14.2** | **22.5** |
| የካፒታል ወጪ ከጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት በጊዜው የገበያ ዋጋ የሚኖረው ድርሻ (በመቶኛ) | **11.8** | **15.8** |
| **የኑሮ ደህንነት ሁኔታ** | | |
| ከአጠቃላይ የድህነት መስመር በታች የሚኖረው ሕዝብ ብዛት (በመቶኛ) | **39** | **29** |
| ከምግብ ድህነት መስመር በታች የሚኖረው ሕዝብ ብዛት (በመቶኛ) | **38** | **28** |
| **ግብርና** | | |
| የግብርና ጠቅላላ ተጨማሪ እሴት እድገት (በመቶኛ) | **13.4** | **6.2 (ዓመታዊ አማካይ)** |
| ግብርናና ተዛማጅ ዘርፎች ከጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት (GDP) የሚኖረው ድርሻ | **46.2** | **43.9** |

| ዘርፍ/ግብ ወይም አመልካች | በ1997 መጨረሻ የተደረሰበት | የ5 ዓመቱ ዕቅድ ግብ (በ2002 መጨረሻ የሚደረስበት) |
|---|---|---|
| ዋና ዋና የሰብል ምርት (በሚሊዮን ቶን) | 16.7 | 38.2 |
| የስጋ ምርት (በ1000 ሜትሪክ ቶን) | 566 | 837 |
| የስጋ ወጪ ንግድ (በ1000 ሜትሪክ ቶን) | 8 | 62 |
| **ኢንዱስትሪ** | | |
| የኢንዱስትሪ ተጨማሪ እሴት ዕድገት (በመቶኛ) | 8.1 | 11.5 (ዓመታዊ አማካይ) |
| ኢንዱስትሪ ከጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት የሚኖረው ድርሻ (በመቶኛ) | 13.4 | 16.5 |
| **ትምህርት** | | |
| የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ሽፋን (ከ1-8) (GER) | 79 | 100 |
| የአንደኛ ደረጃ ትምህርት የማጠናቀቅ መጣኔ (በመቶኛ) | 34 | 63 |
| በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ሴቶች ከወንዶች ያላቸው ጥምርታ | 0.84 | 0.97 |
| የተማሪ መጻሕፍት ጥምረት | 2:1 | 1:1 |
| የተማሪ ክፍል ጥምርታ | 1:69 | 1:50 |
| የ1ኛ ክፍል የማቋረጥ መጠን (በመቶኛ) | 22.4 | 6.3 |
| **ጤና** | | |
| የጤና አገልግሎት ሽፋን (በመቶኛ) | 70 | 100 |
| የዲ.ፒ.ቲ. 3 ክትባት ሽፋን (በመቶኛ) | 61 | 80 |
| የሕፃናት ሞት መጣኔ | 77/1,000 | 45/1,000 |
| የእናቶች ሞት መጣኔ | 871/100,000 | 600/100,000 |
| የወሊድ መቆጣጠሪያ ተጠቃሚዎች መጠን (በመቶኛ) | 15 | 80 |
| የኤች አይ ቪ/ ኤድስ ተጠቂዎች መጠን - (በመቶኛ) | 0.56 | 0.52 |
| በሰለጠነ የጤና ባለሙያ ክትትል ታግዘው የሚወልዱ እናቶች መጣኔ (በመቶኛ) | 9 | 32 |
| **ውሃ** | | |
| የንፁህ መጠጥ ውሃ ሽፋን (በገጠር) በ1.5 ኪ.ሜ ርቀት | 35 | 80 |
| የንፁህ መጠጥ ውሃ ሽፋን (በከተማ) በ0.5 ኪ.ሜ ርቀት | 80 | 92.52 |
| **መንገድ** | | |
| የመንገድ ሽፋን (ኪ.ሜ/1000 ካ.ሜ) | 33.2 | 54.1 |
| በጥሩ ሁኔታ ላይ ያለ መንገድ መጣኔ (በመቶኛ) | 64 | 84 |
| ለሁሉም የአየር ፀባይ ከሚሆን መንገድ ለመድረስ የሚወሰደው ጊዜ (በሰዓት) | 5 | 3.2 |
| መብራት (ኤሌክትሪክ) | | |

| | | |
|---|---|---|
| የመብራት አገልግሎት ሽፋን (በመቶኛ) | 16 | 50 |
| የመብራት አልግሎት ተጠቃሚ ከተሞች (በቁጥር) | 648 | 6,000 |
| **ቴሌኮሙኒኬሽን** | | |
| የቴሌፎን አገልግሎት ሽፋን (በ5 ኪ. ሜ) (በመቶኛ) | 6 | 100 |
| የቴሌፎን አገልግሎት የሚያገኙ ቀበሌዎች (በቁጥር) | 3,000 | 15,000 |
| የሞባይል ተጠቃሚዎች ዴንሲቲ (በመቶኛ) | 0.56 | 8.1 |
| የመደበኛ ስልክ ተጠቃሚዎች ዴንሲቲ (በመቶኛ) | 0.85 | 3.87 |
| የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት በአቅራቢያው የሚያገኝ ሰው (በመቶኛ) (በ5 ኪ/ሜትር ራዲየስ ውስጥ) | 6 | 160 |
| የመደበኛ ስልክ ተጠቃሚዎች ብዛት (በሚሊዮን) | 0.62 | 3.23 |
| የሞባይል ስልክ ተጠቃሚዎች ብዛት (በሚሊዮን) | 0.411 | 6.761 |
| የኢንተርኔት አገልግሎት ተጠቃሚዎች ብዛት (በቁጥር) | 17,375 | 193,100 |
| **ማዕድን** | | |
| የጂኦሎጅ ካርታ ሽፋንን ማሳደግ (በመቶኛ) | 38 | 53 |
| የሀይድሮጂኦሎጂ ሽፋንን ማሳደግ (በመቶኛ) | 27 | 42 |
| የኢንጅነሪንግ ጂኦሎጂ ሽፋንን ማሳደግ (በመቶኛ) | 7 | 15 |
| የጂኦፊዚክስ ሽፋንን ማሳደግ (በመቶኛ) | 65 | 80 |
| **ከተማ ልማት** | | |
| የከተማ ሥራ አጥነትን መቀነስ (ከ50000 በላይ የሕዝብ ብዛት ባላቸው ከተሞች) (በመቶኛ) | 40 | 20 |
| መጠለያና መሠረታዊ አገልግሎቶችን ማቅረብ (በመቶኛ) | 30 | 65 |
| አዳዲስ የመኖሪያ ቤቶች ግንባታ በቁጥር | - | 100,000 (ዓመታዊ አማካይ) |
| የመሬት መሠረተ ልማትና አገልግሎት አቅርቦት መጠን | - | 3,800 ሄክታር (ዓመታዊ አማካይ) |
| የተጎዱና የተጨናነቁ አካባቢዎችን መቀነስ (በመቶኛ) | 70 | 35 |
| የአነስተኛና ጥቃቅን የንግድ ተቋማትን ማሳደግ (በቁጥር) | - | 12,000 (ዓመታዊ አማካይ) |
| **የውጪ ንግድ** | | |
| የግብርና ምርቶች ኤክስፖርት ገቢ (በሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር) | 546 | 1515 |
| የኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ ኤክስፖርት ገቢ (በሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር) | 63.73 (ቆዳና የቆዳ ውጤቶች) | 500 |
| ከማዕድን ዘርፍ የሚገኘውን ገቢ ማሳደግ (በሚሊዮን የኢትዮጵያ ብር) | 20 | 44.7 |

**አባሪ 2:** <u>**የመንገድ ዘርፍ የ5 ዓመት የልማት ዕቅድ ግቦች**</u>

| ዓላማዎች | አመልካቾች | በ1997 የተደረሰበት | የመጀመሪያ ዓመት 1998 | ሁለተኛ ዓመት 1999 | ሦስተኛ ዓመት 2000 | አራተኛ ዓመት 2001 | አምስተኛ አመት 2002 | የማረጋገጫ ምንጮች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. የመንገድ ማዳረስ (Increased accessibility) | ክረምት ከበጋ ከሚያስኬድ መንገድ ላይ ለመድረስ የሚፈጀውን ሰዓት መቀነስ (በሰዓት) | 5 | 4.9 | 4.5 | 4.1 | 3.6 | 3.2 | የመንገድ ዘርፍ ልማት ሪፖርቶች |
| | ክረምት ከበጋ ከሚያስኬድ መንገድ ከ5 ሰዓት በላይ ርቀው የሚገኙ አካባቢዎችን መቀነስ (በመቶኛ) | 72 | 71 | 69 | 67 | 63 | 59 | የመንገድ ዘርፍ ልማት ሪፖርቶች |
| | ክረምት ከበጋ ከሚያስኬድ መንገድ ከ2 ሰዓት በላይ ርቀው የሚገኙ አካባቢዎችን መቀነስ (በመቶኛ) | 88 | 87 | 86 | 85 | 83 | 81 | የመንገድ ዘርፍ ልማት ሪፖርቶች |
| 2. የመንገድ ጥግግትን ማሳደግ (Increased road network density) | የመንገድ ጥግግት የሕብረተሰብ መንገዶችን ጨምሮ (ኪ.ሜ/1000 ካሬ ኪ.ሜ) | 33.6 | 34.9 | 37.8 | 41.7 | 47.5 | 54.1 | የመንገድ ዘርፍ ልማት ሪፖርቶች |
| | የመንገድ ጥግግት የሕብረተሰብ መንገዶችን ጨምሮ (ኪ.ሜ/1000 ሰዎች) | 0.51 | 0.51 | 0.54 | 0.59 | 0.65 | 0.72 | የመንገድ ዘርፍ ልማት ሪፖርቶች |
| 3. የመንገድ አውታር ሁኔታ | ተቀባይነት ባለው ሁኔታ የሚገኝ የመንገድ አውታር ድርሻ | 64 | 66 | 71 | 75 | 80 | 84 | የመንገድ ዘርፍ ልማት ሪፖርቶች |
| | ከጠቅላላ የመንገድ ልማት በጀት ለጥገና የሚመደበው በጀት ድርሻ | 22 | 24 | 26 | 28 | 30 | 32 | የመንገድ ዘርፍ ልማት ሪፖርቶች |
| 4. አዲስ የሚገነቡ መንገዶች | አዲስ የሚገነቡ የፌዴራል እና ክልል ዝቅተኛ መንገዶችን ጨምሮ ርዝመት (በኪ.ሜ) | 552 | 1367 | 3160 | 4362 | 6354 | 7214 | የፕሮጀክት ሪፖርቶች |
| 5. የግሉ የኮንስትራክሽን ዘርፍ በመንገድ ልማት ላይ ያለውን ተሳትፎ ማሳደግ | በመንገድ ግንባታ እና ጥገና የግሉ ዘርፍ ድርሻ (%) | 60 | 75 | 80 | 85 | 85 | 85 | የአፈፃፀም ሪፖርት |
| 6. የትራፊክ እና ሸቀጦች እንቅስቃሴን ማሳደግ | አማካይ የተሽከርካሪዎች ዓመታዊ ጉዞ ርዝመት (በሚሊዮን ኪ.ሜ) | 5.604 | 5.884 | 6.178 | 6.487 | 6.811 | 7.151 | የትራፊክ እንቅስቃሴ ጥናት ሪፖርቶች |

## አባሪ 3: የአንደኛ ደረጃ የትምህርት ልማት ግቦች

| ግብ | አመልካቾች | 1997 | 1998 | 1999 | 2000 | 2001 | 2002 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የአንደኛ ደረጃ የትምህርት ተሣትፎን ማሳደግ | በአንደኛ ደረጃ አንደኛ ሳይክል የንጥር ተሳትፎ* መጣኔ (Net Enrollment Rate) | **67.6** | **70.6** | **74.6** | **78.6** | **82.6** | **86.6** |
| | ሴት | **65.1** | **68.3** | **72.3** | **76.3** | **80.3** | **84.3** |
| | ወንድ | **69.9** | **72.9** | **76.9** | **80.9** | **84.9** | **88.9** |
| | በአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል የንጥር ተሳትፎ* መጣኔ (Net Enrollment Rate) | **33.9** | **39.9** | **45.8** | **51.8** | **57.8** | **63.8** |
| | ሴት | **29.4** | **35.3** | **41.3** | **47.3** | **53.3** | **59.3** |
| | ወንድ | **38.3** | **44.0** | **50.0** | **56.0** | **62.0** | **68.0** |
| የትምህርት ማቋረጥን መቀነስ | አንደኛ ክፍል ትምህርት ማቋረጥ መጣኔ | **22.4** | **19.1** | **15.9** | **12.7** | **9.5** | **6.3** |
| የአንደኛ ደረጃ ትምህርት የማጠናቀቅ መጣኔን ማሳደግ | 5ኛ ክፍል ትምህርት የማጠናቀቅ መጣኔ | **57.4** | **78.4** | **77.8** | **88.7** | **121.1** | **136.6** |
| | 8ኛ ክፍል ትምህርት የማጠናቀቅ መጣኔ | **34.0** | **39.0** | **42.0** | **45.0** | **58.0** | **63.0** |
| በአንደኛ ደረጃ የመምህርና የተማሪ ጥምርታ (Pupil/ Teacher Ratio) መቀነስ | አንደኛ ደረጃ አንደኛ ሣይክል **(1-4)** | **71** | **69** | **65** | **61** | **58** | **63** |
| | አንደኛ ደረጃ ሁለተኛ ሣይክል **(5-8)** | **55** | **55** | **52** | **50** | **47** | **45** |
| | ሁለተኛ ደረጃ **(9-12)** | **78** | **70** | **63** | **55** | **48** | **40** |
| በዋና ዋና የትምህርት ዓይነቶች የመፅሐፍት አቅርቦትን ማሻሻል | የመማሪያ መፃሕፍትና የተማሪ ጥምርታ (Pupil /Textbook ratio) | **2:1** | **1.5:1** | **1:1** | **1:1** | **1:1** | **1:1** |

---

* የአንደኛ ደረጃ ንጥር ተሳትፎ የሚያመለክተው በአንደኛ ደረጃ የመማሪያ ዕድሜ ክልል ውስጥ ካሉ ሕጻናት (ከ7-14 ዕድሜ ክልል) መካከል አንደኛ ደረጃ ትምህርት እየተከታተሉ የሚገኙትን ተማሪዎች ድርሻ ነው።

## አባሪ 4: የጤና ዘርፍ ልማት ዓመታዊ ግቦች

| አመልካቾች | በ1997 የሚገኝበት | የ2002 ግቦች |
|---|---|---|
| የሕፃናት ሞት | 97/1000 በ1996 ዓ.ም | 45/1000 |
| ዕድሜያቸው ከ5 ዓመት በታች የሆኑ ህጻናት ሞት | 140/1000 በ1996 ዓ.ም | 85/1000 |
| የእናቶች ሞት | 871/100000 በ1996 ዓ.ም | 600/100000 |
| የሣንባ ነቀርሳን የመፈወስ መጣኔ | 76% | 85% |
| የዲፒቲ 3 የክትባት ሽፋን (በመቶኛ) | 70 | 80 |
| የወሊድ መቆጣጠሪያ ተጠቃሚዎች መጣኔ | 15% | 60% |
| በሰለጠኑ የጤና ባለሙያዎች ክትትል የሚወልዱ እናቶች መጣኔ | 9% | 32% |
| የተመላላሽ ህክምና የነፍስ ወከፍ አገልግሎት | 0.3 | 0.6 |
| በወባ በተጋለጡ አካባቢዎች 2 አጎበር የሚጠቀሙ ቤተሰቦች መጣኔ (በመቶኛ) | 1 | 100 |
| የጤና ባለሙያዎችና ሕዝብ ጥምርታ (ዶክተር/ሕዝብ) | 1:26¸527 | 1:2¸500 |
| የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞችና የሕዝብ ጥምርታ | 1:25¸000 | 1:2¸500 |

## አባሪ 5: የውሃ ሀብት ልማት ዕቅድ ግቦች

| | 1998 | 1999 | 2000 | 2001 | 2002 |
|---|---|---|---|---|---|
| የንጹህ ውሃ መጠጥ አቅርቦት (ከጠቅላላ ህዝብ በመቶኛ) | 51.5 | 60.4 | 68.8 | 76.8 | 84.5 |
| የገጠር መጠጥ ውሃ አቅርቦት የሚያገኝ ሕዝብ (በ1.5 ኪ.ሜ ክልል) (በመቶኛ) | 44 | 53 | 62 | 71 | 80 |
| የከተማ መጠጥ ውሃ አቅርቦት የሚያገኝ ሕዝብ (በ0.5 ኪ.ሜ.ክልል) (በመቶ) | 80.6 | 83.5 | 86.1 | 89.2 | 92.5 |
| መካከለኛና ከፍተኛ የመስኖ ልማት ግንባታ (በሄ/ር) | 72,550 | 116,432 | 63,088 | 43,965 | 23,645 |
| የተሻሻለ ኦፕሬሽንና ጥገና (በገጠር አገልግሎት የማይሰጡ የውሃ ምንጮች) | 30 | 25 | 20 | 15 | 10 |

## አባሪ 6፡ በልማት ዕቅዱ የተመረጡ የቴሌኮም ዘርፍ ግቦች

| አመልካች | መነሻ ዓመት (1997) | በ5 ዓመቱ መጨረሻ የሚደረስበት (2002) |
|---|---|---|
| በ5 ኪ/ሜ ርቀት የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት የሚያገኝ ህዝብ መጣኔ (በመቶኛ) | 13 | 100 |
| የመደበኛ ስልክ ለደንበኛ የሚያገናኝ መስመር መጣኔ | 0.85 | 3.87 |
| የሞባይል ስልክ ለደንበኛ የሚያገናኝ መስመር መጣኔ | 0.56 | 8.1 |
| የኢንተርኔት አገልግሎት ደንበኞች ቁጥር | 17,375 | 193,100 |
| ስልክ መስመር ያለባቸው ቀበሌዎች ብዛት (ቢያንስ 5 መስመር) | 3,000 | 15,000 |

ማስታወሻ

- የመደበኛና የሞባይል ዴንሲቲ በኢኮኖሚው ዕድገት ትንበያ (GDP) ላይ የተመረኮዘ ነው፡፡
- የቴሌፎን አገልግሎት ያለባቸው ቦታዎች የወረዳ ከተሞች፣ ት/ቤቶች፣ የቴሌኮም አገልግሎት ጣቢያዎችንና የገጠር ቀበሌዎችን ያካትታል፡፡
- እያንዳንዱ አገልግሎት መስጫ ቦታ ከ5 – 30,000 የደንበኛ አቅም ይኖረዋል፡፡

## የምዕተ ዓመቱ የልማት ዓላማዎች

ዓላማ 1: የከፋ ድህነትንና ረሃብን ማስወገድ

ዓላማ 2: የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን ለሁሉም ማዳረስ

ዓላማ 3: የጾታ እኩልነትን መደገፍና የሴቶችን መብት ማስከበር

ዓላማ 4: የህጻናትን ሞት መጠን መቀነስ

ዓላማ 5: የእናቶችን ጤና ማሻሻል

ዓላማ 6: ኤድስን፣ ወባንና ሌሎች በሽታዎችን ለማስወገድ መታገል

ዓላማ 7: የተስማማሚ አካባቢን ዘላቂነት ማረጋገጥ

ዓላማ 8: ዓለምአቀፋዊ የልማት ትብብርን ማጎልበት

## Millennium Development Goals

**Goal 1:** **Eradicate extreme poverty and hunger**

**Goal 2:** **Achieve universal primary education**

**Goal 3:** **Promote gender equality and empower women**

**Goal 4:** **Reduce child mortality**

**Goal 5:** **Improve maternal health**

**Goal 6:** **Combat HIV/AIDS, malaria and other diseases**

**Goal 7:** **Ensure environmental sustainability**

**Goal 8:** **Develop a global partnership for development**

## ፓኔ ምንድን ነው

ፖቨርቲ አክሽን ኔትወርክ ኦፍ ሲቪል ሶሳይቲ ኢን ኢትዮጵያ (ፓኔ) የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ መርሃ ግብሮች እና ተዛማጅ የፖሊሲ ቀረጻና ትግበራ ሂደቶች የታለመላቸውን ግብ በሚያሳካ መልኩ እንዲቃኙ፣ በዚህም ሂደት ውስጥ የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት እና መላው ሕዝብ የጎላ ተሳትፎ እንዲኖረው የማድረግ ዓላማ አንግቦ የተቋቋመ በድህነት ቅነሳ ዙሪያ የሚሰሩ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ጥምረት መረብ (Network) ነው፡፡

ፓኔ ዓላማውን እውን ለማድረግ ጥናትና ምርምር፣ የፖሊሲ ውይይት፣ ይፋዊ የቅስቀሳ ድጋፍ (Advocacy) እና የመረጃ ልውውጥ በማካሄድ እንዲሁም የጥምረት መረቡን በማጠናከር ይንቀሳቀሳል፡፡ ‘‘ድህነት በቃን’’ በሚል መርህ የሚንቀሳቀሱ የሲቪል ማህበረሰብ አቀንቃኞችን በአንድ የጋራ ራዕይ ለጋራ ዓላማ ያሰባሰበው አገር አቀፉ የጥምረት መረብ፣ በተለያዩ የአገሪቱ ክልሎች ራዕይና ዓላማውን በመጋራት የተሰባሰቡ ፓኔ መሰል የክልል ምዕራፎች (Regional Chapters) አሉት፡፡

## የፓኔ ራዕይ

የፓኔ ራዕይ ፍጹም ድህነት ተወግዶ ዜጎቿ ነጻነታቸውና ማንነታቸው ተከብሮ የሚኖሩባት ኢትዮጵያን ማየት ነው፡፡

## የፓኔ ተልዕኮ

ፓኔ ድህነት ተወግዶ ዘላቂ ልማትና ዕድገት እውን እንዲሆን ዜጎች በፖሊሲ ቀረጻ፣ ትግበራ፣ ክትትልና ግምገማ ሂደቶች ላይ የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርጉ በማብቃት፤ የድሆች ድምጽ በውሳኔ ሰጪዎች ዘንድ ተሰሚነት እንዲያገኝ፣ እንዲሁም የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ መንግስት እና ለጋሾች ለድሃው ሕዝብ ይበልጥ ተጠያቂነት እንዲኖራቸው ለማስቻል ይንቀሳቀሳል፡፡

## የፓኔ ዓላማዎች

ዋና ዋና የፓኔ ተቋማዊ ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ድሀ ተኮር የልማትና ድህነት ቅነሳ ፖሊሲዎች እንዲቀረጹና በተገቢው መንገድ እንዲተገበሩ ማበረታታት፣

- በፖሊሲ ቀረጻ፣ ትግበራና ግምገማ ሂደቶች የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማትና ድርጅቶች በንቃት እንዲሳተፉ ማስቻል፣
- የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በሚንቀሳቀሱባቸው አካባቢዎች ያሉ የማህበረሰቡ አባላትና የተረሱ ወገኖች ድምጻቸው ጎልቶ እንዲሰማና ጉዳያቸው በፖሊሲ ቀረጻ አጀንዳ ውስጥ እንዲካተት በሚያደርጉት ጥረት አቅማቸውን ማጠናከር፣
- የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት/ድርጅቶች ከመንግስትና ከለጋሽ ድርጅቶች ጋር ያላቸውን አጋርነት ማጠናከር፣
- ማህበረሰብ አቀፍ ድርጅቶች እንዲሁም የወረዳና ቀበሌ መስተዳድር አካላት በድህነት ቅነሳው ጥረት ውስጥ በንቃትና በትጋት መንቀሳቀስ እንዲችሉ አቅማቸውን ማጎልበት፡፡


<u>**አድራሻ**</u>

ፖቨርቲ አክሽን ኔትወርክ ኦፍ ሲቪል ሶሳይቲ ኦርጋናይዜሽንስ ኢን ኢትዮጵያ (ፓኔ)

ስልክ፡

+251-011- 663 59 65
+251-011- 663 94 28

**ፋክስ**: +251-011- 663 96 79
**ፖ.ሣ.ቁ**: 2433 **ኮድ** 1250
**ኢ ሜይል**: pane@ethionet.et
**ድረ ገጽ** : www.pane.org.et
**አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ**